# ድምፁ የታፈነና የተረሳ ወገን።   (ከጐሹ ገብሩ ለይኩኖ መስፍን)

አቶ ይኩኖ መስፍን ከቁጥር አንድ እስከ ቁጥር አራት ˜ፍትሕ የጠማው ሕዝብ˜ በሚል ርዕስ ባስነበቡን ጹሁፍ ፤ በበኩሌ የምገመግመው በጣም የተዋጣለትና እንከን የሌለው እንደሆነ ነው። ሌሎችም እርሶን የመሳሰሉ ትግራይ ተወልደው ያደጉ ፤ የወያኔን አረመኔነት ከፍጥረቷ እስከ አሁን ያለችበት ሰዓት ድረስ በመላው ኢትዮጵያ በተለይም በትግራይ ሕዝብ ላይ ያደረሰችውና እየፈፀመችው ያለውን አርመኔያዊና አሰቃቂ ደርጊት ለሚመለከተው ወገን ሀቁን ማጋለጥ አሁን ላለው ሆነ ለተተኪው ትውልድ የታሪክ ፀጋን ያጐናጽፋል። በዚህ ባሳለፍናቸው 37 የጭቆና ዓመታት ወያኔ በሀገራችንና በሕዝባችን ያደረሰችው አሁንም እያደረሰችው ያለውን ዘግናኝና አረመኔያዊ ተግባራት ስትፈጽም በዓይነ ሕሊናው የተመለከተ ሁሉ፡ የሰላም እንቅልፍ ተኝቶ የሚያደር ይኖራል ብዬ አላምንም።

እንዲያው ቀላል ምሳሌ ብጥቀስ፡ ከስኒማ ቤት ሄጀ የምመለከተው ድራማ አሰቃቂና ጭካኔ ያዘለ ትርኢት ከሆነ ለሊቱን ሁሉ ያ ያየሁት ሁሉ ሀቅ መስሎኝ ስባንን  ነው የማድረው። ስለዚህ ወያኔ መላውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ አማቃና ረግጣ ማሰቃየቷን እያወቁ እንደማያውቁ ሆነው ህሊናቸውን ሸጠው አላየሁም አልሰማሁም የሚሉን ሁሉ የሰላም እንቅልፍ ተኝተው የሚያድሩ አይመስለኝም። ድፍረቱና ብርታቱን ሰጥቷቸው መተንፈስ ከቻሉ ግን የህሊና እረፍትና በተበደለው ሕዝብ ዘንድም ወገናዊ ባለውለታ ሆነው እንደሚታዩ ለሰከንድም ጥርጣሪ የለኝም። እውነትን ተናግሮ ከመሸበት ማደር የሚሉት የአበው ተረት ትክክለኛነቱ እዚህ ላይ ይመስለኛል። በጥቂቱ ይህን ካልኩኝ ዘንዳ ወደ ዋናው የተነሳሁበት አርዕስቴ ማለትም ገና ስላልተነገረለትና በወያኔ ሥርአት ድምፁ ታፍኖ እንዲረሳና ብሎም ዘሩ እንዲጠፋ  ስለተፈረደበት  ወገኔ ጉዳይ ልመልስዎት።

በቅድሚያ በዚህ አጭር ማስታወሻዬ ላይ ግልጽ ላደርግልዎት የፈለኩት ሃሣብ ወያኔ የወልቃይት ጠገዴ መሬትና ማህበረሰብ ወደ ትግራይ ማካተቷን በመቃወም የሚቀርቡትን የተቃውሞ ድምፆች በማስመልከት ˜በፅሁፍዎ 4ተኛና የመጨረሻ ክፍል  ላይ በገፅ 6 የመጨረሻ አንቀፅ ውስጥ` የሰጡትን ማብራርያ በግልጽ መታረም ያለበትና የተሸፈነውን የወያኔ ተንኮል የወለደውን <u>የወልቃይት ጠገዴን  ሕዝብ አጥፍቶ (በትግራይ) ህዝብ የመተካት</u> (ethnic cleansing)ወንጀል እርስዎን ከመሰለ ለእውነት ቁሜ አለሁ ከሚል ሰው ይቅርና ወገን ከወገን ጋር በማጋጨት ብሎም በማጣላት የስልጣን እድሜውን ለማራዘም ተንኮል ሲቀይስ የሚያድረው አቶ መለሰም ሊያስተባብለው ያለሞከረውና ዛሬም ከ20 ዓመት የመንግስትነት ስልጣን በኋላም ቢሆን ˜የትግራይ ነፃ አውጪ` በመሆን በስፋትና በጥልቀት የሚፈጽመው አኩይ ወንጀል ጭምር መሆኑ ነው።

ውድ አቶ ይኩኖ፡ እርሶ በተከታታይ ያወጡትን ጽሑፎች ተጠቅመው በአጠቃላይ ወያኔ በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ እየፈጸመችው ያለውን ዘርፈ ብዙ ወንጀሎችን ለመግለፅ ሞክረዋል። በተለይም በትግራይ አካባቢ ወያኔ ያደረስችውን በደል ከበረሃ ጀምሮ ቤተመንግሥቱን እስከ ተቆጣጠረችበት ወቅት ያዩትንና የሰሙትን እንዲያውም አንዳንዱን ማለት እርሶ በተወለዱበት አካባቢ በሽሬ እንዳስላሴ የነበረውን የውሃ እጥርት በፎቶግራፍ የተደገፈ ማስረጃ በማቅረብ ሰፋ አድርገው በመዘገብዎ አበጀህ እንጂ ˜መንደርተኛ` ወይም ˜ጎጠኛ` ብሎ የወቀስዎት ግለሰብ ይሁን ድርጅት ይኖራል

ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ወያኔ በተለያዩ አካባቢዎች የምትፈጽማቸውን ድርጊቶች ማጋለጥ ትምክህተኞች ወይም ጽንፈኞች ብሎ መደምደም ፍትሃዊና አግባብ አይመስለኝም የበደል ትልቅና ትንሽ የለውምና። በዚህ አጋጣሚ ባለፉት ተከታታይ ጽሑፎቾ የመጨረሻውን ጨምሮ እንደሚያሳየው የውሃ እጥረት ሆነ የኑሮ ውድነት ያጠቃው ወገናችን አስቸኳይ መፍትሄ እንዲያገኝ ከልብ እመኝለታለሁ።

አቶ ይኩኖ እስኪ አንድ አፍታ ልጠይቆዎት ፤ በጐንደር አካባቢ የተወለዱ ኢትዮጵያዊያን ዜጎች በዘረኛው የወያኔ ወራሪ ቡድን እየደረሰባቸው ያለውን አድሎና የግፍ አገዛዝ ፣ እርሶን ለመሰለና በሌላኛው የሃገሪቱ ክፍል ለተወለደ ኢትዮጵያዊ ማሳወቅና ማስረዳት እንዴት ብሎ ነው የትግራይን ሕዝብ ታሪክ አጉዳፊና ክብር ነኪ የሚሆነው? ˜ወልቃይት ወደ ትግራይ ተወሰደ ተጠቃለለ ብላችሁ ያዙን ልቀቁን ትላላችሁ ከትግራይ መሬት ተቆርሶ ወደ አፋር የተከለለው መሬት በሚመለከት ግን አንድም ቀን ትንፍስ ብላችሁ አታውቁም™ የሚል አድሎ ያለበት ኃይለ-ቃል የተሞላበት አስተያዬትዎ ግን አልተስማማሁበትም። የትግራይ መሬት ያለ አግባብ ወደ አፋር ተወስዷል የሚሉ ከሆነም ይህንን በደል በለመደው እጅዎ ወደኤርትራ የሄዱትንም ጨማምረው በክፍል 5 ቢመለሱበት መልካም ይመስለኛል፡፡ ነገር ግን **የመሬት መወሰድና የዘር ማጥፋት ወንጀል** ምን አገናኘው? እኛ እኮ እያልን ያለነው በግልፅ ቋንቋ ዘራችን እየጠፋ ነው! ይልቅስ ይህ አካሄድዎ ˜ከባልሽ ባሌ ይበልጣል™ የሚለውን ያገሬን ተረት በትልቁ ያስታውሰኛል፡፡

እንደ እኔ ሃሳብ ከሆነ ግን የእኔና የእርሶ ግንኙነት በትልቁ ደግሞ የጎንደርና የትግራይ ህዝቦች ኩታ ገጠም በሆነው ድንበራችን ፣ በሽቀጣ ሽቀጥ ልውውጦሽ ፣ አንዱ ያመረተው ለሌላው በመሻሻጥ ፣ ባጠቃላይ የንግድ ዝውውርና መሰረታዊ ትስስራችን ኢትዮጵያዊነት እንጅ ፣ የወልቃይት ጠገዴ አስተዳደሩም ሆነ ባሕላዊ ቁርኝቱ ከክፍለ ሀገሩ ከጐንደር እንጅ ከትግራይ ጋር እንዳልሆነ እርስዎም ይጥፋዎታል የሚል እምነት ባይኖረኝም በዚህ መጣጥፌ ላይ ግን ዛሬ ይህንን ታሪካዊ ሃቅ አበክሬ ላረጋግጥልዎት እወዳለሁ። እኔ እስከማውቀው ድረስ የወልቃይት ሕዝብና የትግራይ ሕዝብ ተከባብሮና ተመሳስሎ የሚኖር የሁለት ክፍለ ሀገር ሕዝብ እንደሆነ ብቻ ነው።

አቶ ይኩኖ የትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ግንባር (ወያኔ) ሲፈጠር እነ አቶ ስብሐት ነጋ ፣ መለስ ዜናዊና የጥፋት ተባባሪዎቻቸው ያልነበረ ታሪክ ፈጥረው ታላቋን ትግራይ ለመመስረትና ቆዳዋን ለማስፋት ብሎም ከኢትዮጵያ ለመገንጠል በታሪክ የትግራይ ሆኖ የማያውቀውንና በተፈጥሮው ታሪካዊና ለም የሆኑትን የጎንደር መሬቶች ጠለምት ፣ ወልቃይትና ጠገዴን ቀምቶ በመውሰድ የትግራይ ማደረግና ወደ ሱዳን እንደ ልብ ለመግባትና ለመውጣት እንዲያመቻቸው ሲሉ ያደረጉት ወረራ መሆኑና ወያኔ በ1968ኢ.ም ባወጣው ማኒፌስቶ በግልፅ መቀመጡን አይርሱብን እንጂ! በርስዎ አባባል መንግስት (በ1983ኢ.ም ወያኔ ስልጣን ያዘች) ለአስተዳደር እንዲያመቸው የተደረገ የመሬት ማሽጋሸግ ነው ይበሉን? አይን ያወጣ ሽፍጥ አይሆንብዎትም እንዴ? ለነገሩማ የወልቃይትን ጉዳይ አድበስብሶ እንዲህ ማለፍ የርስዎ ብቻ ችግር እንዳልሆነ የብዙዎች ከወያኔ ጋር የተጣሉ የትግራይ ተወላጆችም እምነት ጭምር መሆኑን በተደጋጋሚ አይተናል። የእርስዎ ያን ሁሉ የወያኔን ወንጀልና ግፍ ዘርዝረው እዚህ ላይ ሲደርሱ ˜ወገቤን™ ማለትዎና በሃሳብም ቢሆን ከግፈኞች ወገን መጨመርዎ በእጅጉ ያሳዝናል!ያስቆጫልም!

ወንድም አቶ ይኩኖ እስኪ የምንለውን እየተሆነ ያለውን እውነታውን ይስሙን ጓደኞችዎንም ያሰሙልን (አዉቆ የተኛ ቀስቃሽ የለውም እንዳይሆንብን እንጂ)

1ኛ. ወያኔ የወልቃይት ጠገዴ ወንድ ፣ ሴት ፣ ህፃን ፣ ሽማግሌ ሳትለይ እያጠፋቻቸውና አሁንም መንግሥትነት ከጨበጠች በኋላ እያደረሰችው ያለ ማለቅያ ያጣ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ነው እያሳሰበንና እያስጨነቀን ያለ እንጅ የትግራይ ሕዝብ እንደ ኢትዮጵያዊነቱ የትም ሂዶ መኖር የለበትም ብሎ የተቃወመ ግለሰብም ሆነ ማሕበረሰባዊ ተቋም የለም። ወያኔና ግብረአበሮቿ ግን ደማችን አፍስስን አጥንታችንን ከስክሰን ያገኘነው መሬት በማለት፡ ለዘመናት የኖረውን ተወላጁን ህብረተሰብ ከቀዬው በማፈናቀል ፣ በመግደል ፣ በማሰር ፣ ትውልድ አገሩን ጥሎ እንዲሄድ በማድረግ ፣ መሬቱ ቀምታ ከትግራይ ብቻ ሆን ብሎ ሰፋሪ በማምጣት የወልቃይትን ንብረት እዲውርስ ሆኗል ፣ እየሆነም ነው። የእኛም ተቃውሟችን ይህንን እኩይ ተግባር ይቁም ፣ በአንፃሩ የወልቃይት ሕዝብ እንደ ሕዝብ በቦታው የመኖር ፣ የመማር ፣ የማረስ ፣ ልጆቹን የማስተማር ብሎም የዲሞክራሲ መብቱ ይጠበቅ ፣ ሰብአዊ መብቱ ይከበር ፣ የአድልዎ አስተዳደር ይቁም ፣ ወያኔ በቆፈረቻቸው የከረሰ ምድር እስር ቤት በግፍ የታሰሩ ወገኖቻችን ይፈቱ ፣ ንፁህ ዜጐች ከመኖርያ ቤታቸው ከሞቀ ኑሯቸው አፍናችሁ በመውሰድ አታጥፉብን አትግደሉብን ወዘተ ነው ያልነው እንጅ ለምን የትግራይ ሰው አገር መራ ፣ ስልጣን ያዘ ብለን አልተቃወምንም።

2ኛ. አያት ቅደም አያቶቻችን ያወጡትን ታሪካዊ የትውልድ ቦታችን የመጠሪያ ስም ማለት ወልቃይት ጠገዴ በምእራብ ትግራይ ፣ የመንደርና የተቁዋማት ስም በትግራዊ ስሞች መተካታቸው አጥብቀን እንቃወማለን። የቆየው ታሪካዊ ባህላችን ፣ ልምዶቻችን ፣ ክብራችን ሊጠበቅ እንጅ ድብቅ አላማ ያለው የወያኔ ቡድን ታሪካችንን እሱ እንደፈለገው የመለወጥ ሆነ የመቀየር መብትም የሞራል ብቃትም የለውም።

3ኛ.ታሪክ ያለምንም ማወላውል እንደሚመሰክረው የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ኢትዮጵያዊ ጐንደሬ እንጅ የትግሬ ዘርነት የለንም ፣ ያለዘራችን ዘር ልትሰጡን ማንነታችን ለማጥፋት አትሞክሩ።

4ኛ. የወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ተወልዶ ባደገበት ቦታ ተዘዋውሮ የመኖር በግብርና መስኩ አርሶ የመብላት መብቱ ይከበር ፣ እንደ ናዚ ጀርመን በአንድ ጠባብ ለእርሻ በማያመች ቦታ አጉሯችሁ ያም ለመቆጣጠር እንዲያመቻችሁ የምታደርጉትን የመሬት አሽቅድድም በጥብቅ እንቃወማለን የሕዝባችን ሙሉ መብቱ እስኪረጋገጥ ድረስም የተጠናከረ ትግል ከማድረግ ወደኋላ እንደማንል ልናረጋግጥላችሁ እንወዳለን።

በመጨረሻም የወልቃትይ ጠገዴ ሕዝብ ችግር የንጹህ ወሃ አቅርቦትና የአንዳንድ ቆሳቁስ እጥረት ብቻ ቢሆን ኖሮማ በመላው አገሪቱ ተስፋፍቶ ያለ ችግር ነው በሚል ማለፊ እንችል ነበር። ወያኔ የወልቃይት ጠገዴን  ሕዝብ ለ37 ዓመት በረቀቀ ዘዴ ከምደረ ገጽ ለማጥፋት ስትስራ የቆየችና ስልጣንን መከታ በማድረግ ይህን ጅግና ኢትዮጵያዊ ዜጋ አሜን ብሎ እዲገዛላትና አንገቱን ደፍቶ እንዲኖር ሌት ተቀን እየጣረች ነው። ዛሬ ታሪክ ነጋሪዎች ፣ ታላላቅ አዛውንቶች ፣ ወኔ ያላቸው ጅግኖች ፣ ሆን ተብሎ እንዲገደሉ ከአገር ተሰደው እንዲጠፉ በብዛት ደግሞ እስር ቤት እንዲማቅቁ ተደርጓል። እኛ የወልቃይት ጠገዴ ተወላጅ ኢትዮጵያዊያን እያልን ያለነው ወያኔ ዘራችንን እያጠፋው ነው ፣ ሥር ነቀል የሆነ የዘር ማጥፋት ወንጀል

እየተፈፀመብን ነው ፣ አንድን ዘር አጥፍቶ በሌላ ዘር የመተካት ዘመቻ ዐይን ባወጣ መልኩ ተጧጥፎ ቀጥሏል ፣ ዜጎች በትውልድ መንደራቸው እንዳይኖሩ እየተደረገ ነው። የወልቃይት ጠገዴ ችግር የሚፈታው የመላው ኢትዮጵያ ችግር ሲፈታ ብቻ ነው ቢባልም የትግራይ ነጻ አውጭ ግንባር በያዘው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ከቀጠለ ነገ ወልቃይት ፣ ጠገዴና ጠለምት የሚባል ካርታም ህዝብም አይኖርም ። ስለዚህ መላው ኢትዮጵያዊ ማለት እርሶንና መሰሎችውንም ጨምሮ ማለት ነው እየደረሰብን ያለውን ኢ-ሰብአዊ ግፍ ተገንዘቦ ከጎናችን ይቁም ፤ ማንም የአገሬ ጉዳይ ያገባኛል የሚል ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ በወልቃይት ጠገዴ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን ዘርፈ ብዙ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ለማስቆም አገር አቀፍ ትብብርን እንሻለን።

በስህተት ወይንም ባለማወቅ አላስፈላጊ ኃይለ ቃል ተጠቅሜ ከሆነ አርማችሁ እንድታነቡልኝ በማክበር እሳሰባለሁ፡፡

ኢትዮጵያ ለዘልዓለም ትኑር!!!

02/07/2012